# ልብ ያለው ፣ ልብ ይበል

ለወያኔ ያደሩ ፣ ወሬ የሚያራግቡ
የሚያዘጠዝጡ ፣ ጡቱን የተጣቡ
በየትርፍራፊው ፣ ሰክረው የጠገቡ
አረቄ አንፍዟቸው ፣ በሆድ የሚያስቡ
ዜጋን ያሳዘኑ ፣ ደም የተቀባቡ
የግፍ ተባባሪ ፣ አላጋጭ በህዝቡ
መሸባችሁ በቃ ፣ ወደ ትግሉ ፣ ግቡ ።
    ለስልጣን ፣ ለገንዘብ ፣ ስትስገበገቡ
    ዘመኑ ተቋጭቶ ፣ ሲዘጋ መዝገቡ
    የነፍስ አባታችሁ ፣ ፍፃሜው መቅረቡ
    አልታይ ካላችሁ ፣ ሊሮጥ ማኮብኮቡ
    መባነን አይቻል ፣ መቃብር ስትገቡ
    ልብ ያለው ፣ ልብ ይበል ፣ ሳይመሽ ነው ፣ ማሰቡ ።

ከደደቢት አውሬ ፣ አብሮ ከመልከስከስ
ነገ ለሚበላህ ፣ አንተም ፣ ቀንህ ሲደርስ
ለሆድህ ከማደር ፣ እርምን ከመቋደስ
ጅቡ ከሚበላህ ፣ በልተኸው ተቀደስ
አጥፊህን በማጥፋት ፣ መቼም አይረከስ ።
    በሆድህ ከማሰብ ፣ ነገ ለምታለቅስ
    የተመካህበት ፣ ጭራሮ ቤት ፣ ሲፈርስ
    አብረህ ከምትጠፉ ፣ አንተም ፣ የትም ላትደርስ
    ፊትህን ፣ ወደ ህዝብ ፣ አድርግ እስቲ ፣ መለስ
    ምሽግ አይሆንህም ፣ ጫንቃህ ፣ ወይም ደንደስ ።




አይንህ ፣ ታውሮብህ ፣ ጆሮህ ተደፍኖብህ
ከደደብ ተዳብለህ ፣ ልብህ ደንድኖብህ
ማስተዋል ተስኖህ ፣ ህዝብ እየመጣብህ
ሆድ አምላኩ ፣ ሆነህ ፣ የርግማን ሆኖብህ
አልቃሽም አታገኝ ፣ ሞትም አያምርብህ ።

    ከሙት ጋር ፣ አብሮ ፣ ሞትን መጠበቁ
    ዘንድሮም ፣ እንደ አምና ፣ መጨመላለቁ
    አልታይ ህ ካለ ፣ ሰዓቱ ማለቁ
    ባያሳዝን እንኳን ፣ አልቀረም ማሳቁ
    ስትጃጃል ማየት ፣ ሙት አቅፎ ፣ መውደቁ ።

ታዛቢው ... November 22/2011